# ማነው እብድ ? የአርበኝነት ካርድ በ 500 ዶላር ከ ስድስት አመት በፊት በአማሪካ ሲቸረችር የነበረ ደላላ

ማነው እብድ ? የአርበኝነት ካርድ በ 500 ዶላር ከ ስድስት አመት በፊት በአማሪካ ሲቸረችር የነበረ ደላላ ድርጅት ወይስ ይህ ድርጅት ጤባ እና ሌባ ነው ብሎ ያጋለጠው ሰው ? ማነው እብድ፥ ኤርትራ በርሃ ገብቶ ታጋይ ለመባል ሲል ብቻ ያለ ምንም ስራ ዝንብ እሽ እያለ አጉል የሆነ ዘመን የሚገፋው ሰው ወይስ በኤርትራ በኩል የሚደረገው ትግል አንድ ጋት ወደፊት የሚወስድ እንዳልሆነ የሚናገረው ? በእውነት ማነው ንክ ? ከዌብ ሳይታቸው መጨናነቅ ፥ በክሊክ ስለሚያገኙት ቢዝነስ ተጨንቀው ቅስም ሰባሪ ዜናን ሳይቀር ሰበር ዜና እያሉ የሚያቀርቡልን ወይስ ሚዛናዊነት እንደሚጎላቸው እና መስተካከል እንዳለባቸው የሚናገረው ? ማነው ሎኮ ፥ ኢሳያስ ከህዝቡ ጋር ነው የሚኖረው ፥ ጀነራሎቹ እግራችንን ሊያጥቡን ነበር ብለው ፥ በታሪክ የምናውቀውን ከሳጥናኤልም የከፋውን ሻእቢያ መላእክ አድርጎ ሊያቀርብልን የሚፈልገው ሰው ወይስ ይህ ቀልዳቸው አንገሽግሾት የተፋታቸው ወዳጃቸው ? ማነው እብድ ፥ ከሌንጮ ጋር ተዋህዶ አዲስቷን ኢትዮጵያ እመስርታለሁ ብሎ የሚያስበው ተራ አቅመ ቢስ ተስፈኛ ወይስ የሌንጮን ማንነት በገሃድ የሚናገረው አካል ? እብዱማ ይለያል በግብሩ !

ኄኖክ የሺጥላ